ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (SPS) የ SBIRT ፕሮግራም አካል የሆነውን የራስህን ፈትሽ (Check Yourself) መጠይቅ ለተማሪዎች ይሰጣል።ይህ ፕሮግራም በ King County's Best Starts for Kids initiative የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ሲሆን ዓላማውም የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀምን ለመቀነስ፣የአዕምሮ ጤናን ለማሳደግ እና ለተማሪዎች እድገት የሚያስፈልጉትን ሀብቶች ለማቅረብ ነው።

የራስህን ፈትሽ መጠይቅ ሙሉ በሙሉ በፈቃደኝነት የተመሰረተ ነው።ቤተሰቦች ለተማሪዎቻቸው ላያሳትፉ ይችላሉ፣ተማሪዎችም ጭምር መሳተፍ አልፈልግም ሊሉ ይችላሉ።አለመሳተፍ የሚያስቀጣ ቅጣት የለም እንዲሁም በተማሪዎ ውጤት ላይ ምንም ተፅእኖ የለውም።ጥያቄዎቹን አስቀድመው ማየት ለሚፈልጉ ቤተሰቦች የመጠይቁ ቅጂ ይሰጣል።መጠይቁን አስቀድመው ለማየት ወይም ተማሪዎን ላለመስተፍ ከፈለጉ፣እባክዎን የትምህርት ቤቱን ዋና ፅ/ቤት ያነጋግሩ።

ስለ SBIRT ወይም ስለ ራስህን ፈትሽ(Check Yourself) የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከዚህ በታች ያሉት በተደጋጋሚ የሚነሱትን ጥያቄዎች ይመልከቱ።

---

**SBIRT እና ራስህን ፈትሽ ምንድን ናቸው?**

ማጣሪያ(Screening)፣አጭር ጣልቃገብነት (Brief Intervention) እና ወደ እንክብካቤ መላክ( Referral to Treatment)- (SBIRT) የእፅ አጠቃቀምን ለመለየት፣ለመቀነስ እና የተማሪዎችን አካላዊ፣ስሜታዊ እና ማህበራዊ ደህንነትን ለማሳደግ ጥቅም ላይ ይውላ ል::SBIRT ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት:

- ማጣሪያ (**S**creening): ተማሪዎች ራስህን ፈትሽ("Check Yourself" )ተብሎ የሚጠራውን የ 10-15 ደቂቃ አሳታፊ እና ምቹ የሆነ በድር ላይ የተመሰረተ መጠይቅ የወስዳሉ።ራስህን ፈትሽ ለተማሪው ፈጣን ግላዊ ግብረመልስ ይሰጣል እንዲሁም አንድ ተማሪ ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልገው መሆን አለመሆኑን ለማወቅ ሰራተኞችን ይረዳል።
- አጭር ጣልቃ ገብነት (**B**rief Intervention):አንድ የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሰራተኛ አባል ድጋፍ ከጠየቁ ወይም ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ካሳዩ ተማሪዎች ጋር ይገናኛል።ተማሪው በተማሪው ጥንካሬ እና ችሎታዎች ላይ የሚያተኩር አጭር፣ቀጣይነት ያለው ውይይት ከሰራተኛው ጋር ሊኖረው ይችላል።የእነዚህ ውይይቶች ዓላማ ተማሪዎችን ከወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው እና ሌሎች ድጋፎች ወይም የስኬት ስልቶችን ለማገናኘት ነው።
- ለእንክብካቤ መላክ (**R**eferral To services):ተማሪው ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልገው ከሆነ፣የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን ወደ አግባብነት ያለው ማህበረሰብ ወይም ትምህርት ቤት-ተኮር አገልግሎቶችን ሊመሩ ይችላሉ።

የራስህን ፈትሽ መጠይቅ፣በሲያትል የህጻናት ሆስፒታል የተዘጋጀ እና የተረጋገጡ የማጣሪያ መሳሪያዎችን ያካተተ ሲሆን በጠንካራ ጎኖች ላይ የተመሰረተ የወጣቶች ጤናን ለማሳደግ እና የአደንዛዥ እፅ አጠቃቀምን በመከላከል ላይ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ጠቃሚ ፈጠራ ነው።የኪንግ ካውንቲ ወጣቶች እና ቤተሰቦች በራስህን ፈትሽ ዕድገት ላይ ተሳትፏል፣እና የእነርሱ አስተያየት ሁሉን አቀፍ፣ባህላዊ ምላሽ ሰጪ እና ለወጣቶች ተስማሚ የሆነ መጠይቅን ለማዘጋጀት አስፈላጊ ነበር።

**SBIRT ተማሪዎችን እንዴት ይጠቅማል?**

SBIRT ለተማሪዎች ድጋፍ ለመስጠት የተሳካ፣ንቁ አካሄድ ነው።ተማሪዎች የ SBIRT ፕሮግራም ፍላጎታቸውን የሚገልጹበት አስተማማኝ እና ምቹ መንገድ እንደሰጣቸው ይጠቁማሉ።በተማሪዎች እና በትምህርት ቤት ሰራተኞች መከከል ውይይት እንዲፈጠር ያደርጋል፣ሰራተኞች ድጋፍ እንዲሰጡ እና ተማሪዎች ጤናማ ምርጫ እንዲያደርጉ ያነሳሳል።በ2021-2022 የትምህርት ዘመን ከ1,500 በላይ ተማሪዎች መጠይቁን ወስዷል።ከነዚያ ተማሪዎች 22% የሚሆኑት መጠይቁ ከመውሰዳቸው በፊት በትምህርት ቤቱ ሰራተኞች የማይታወቁ ፍላጎቶች ነበሯቸው።የ SBIRT ፕሮግራም በትንሽ የክፍል መስተጓጎል እና ትንሽ ድጋፍ በመስጠት ሊስተካከሉ የሚችሉ እነዚህን ስጋቶች አስቀድሞ ለመለየት ይረዳል።

**የራስህን ፈትሽ መጠይቅ መውሰድ አማራጭ ነው?**

አዎ! የራስህን ፈትሽ መጠይቅ መውሰድ በፈቃደኝነት ነው።የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች ስለ SBIRT እና ስለ የራስህን ፈትሽ መጠይቅ ለተማሪዎች ያስተዋውቃሉ እንዲሁም የማጣራያው ምክንያት ያብራራሉ። መጠይቁ የሚጀምረው ተማሪዎች ለመሳተፍ ያላቸውን ፈቃድ እንዲያሳዩ በመጠየቅ ነው።ወላጆች / አሳዳጊዎች የትምህርት ቤታቸውን አስተዳደር፣የአማካሪ ቡድኑ፣ወይም የSBIRT ሰራተኛን በማነጋገር ልጃቸውን ላለመሳተፍ ማድረግ ይችላሉ::

**በፕሮጀክቱ ውስጥ የሚሳተፉ የሲያትል ትምህርት ቤቶች የትኞቹ?**

SBIRT ከ2023-2024 የትምህርት ዘመን ጀምሮ በሁሉም አስራ ሁለቱ የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች አጠቃላይ መለስተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ይተገበራል።እንዲሁም የፍራንክሊን እና የኢንግራሃም ሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤቶች የ SBIRT ፕሮግራም ተግባራዊ ያደርጋሉ።

**የራስህን ፈትሽ መጠይቅ (Check Yourself questionnaire) የሚወስዱ ተማሪዎች የትኞቹ ናቸው??**

በተሳታፊ ትምህርት ቤቶች የራስን ፈትሽ መጠይቅ ለ7ኛ፣8ኛ እና 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ይሰጣል።የተመረጡ ትምህርት ቤቶች ሁለንተናዊ የራስህን ፈትሽ መጠይቅ ለ 6ኛ ክፍል ሊሰጡ ይችላሉ።ሁለንተናዊ ፍተሻ (universally screen )የተማሪን ፍላጎት በመለየት እና ምላሽ በመስጠት ሂደት ላይ ያለውን አድልዎ ለመቀነስ እና የባህሪ ጤና አገልግሎቶችን ተደራሽ ለማድረግ ይረዳል።የእራስህን ፈትሽ መጠይቅ አልፎ አልፎ በራሳቸውን መጠይቁ ለመውሰድ ለመረጡ፣ዝቅተኛ አቴንዳንስ ላላቸው፣የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም የስነ-ስርዓት እርምጃዎች ለሚሟላት ወይም በተማሪው መረጃ መሰረት ለሌል ዓላማ ለተመረጡ ተማሪዎች ሊሰጥ ይችላል።

**በራስህን ፈትሽ መጠይቅ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?**
የእራስህን ፈትሽ መጠይቅ አሳታፊ መሳሪያ ነው እና ጥያቄዎቹ በተማሪ ምላሾች ላይ ተመስርተው ይለያያሉ።ስለ ማንነት፣ጥንካሬዎች፣ነባር ድጋፎች፣ ግቦች፣የዕፅ አጠቃቀም፣የአእምሮ ጤና እና ደህንነት የሚጠይቁ ወደ 40 የሚጠጉ ጥያቄዎች አሉ።መጠይቁን ቀድመው ለማየት ለሚፈልጉ ሁሉ  ሲጠይቁ ይሰጣል።

**የራስህን ፈትሽ መጠይቅ የምርመራ መሳሪያ ነው?**
አይ፣የራስህን ፈተሽ መጠይቅ ምርመራ አይደለም።የተማሪው ውጤት ተማሪው ከድጋፍ ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ብቻ ለት/ቤቱ ሰራተኞች ያሳያል።ውጤቱ ተማሪው ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ካሳየ፣የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ውጤቱን ለማረጋገጥ እና ስለ የተማሪው የድጋፍ  ፍላጎት ለመነጋገር ከተማሪው ጋር ይገናኛሉ።ሰራተኞቹ የተማሪውን ቤተሰብ ማነጋገር ወይም ተማሪውን እንደአግባቡ ወደ ሌላ ግብዓቶች እና አገልግሎቶች መላክ ይችላሉ።

**የማጣሪያ ውጤቶች ማን ያያቸዋል?**
መጠይቁ የሚተዳደረው በትምህርት ቤቱ የመከላከል እና የጣልቃገብነት ባለሙያ ነው።ውጤቱን መጀመሪያ የሚገመግመው እሱ ይሆናል።የግለሰቦቹ ምላሾች ከሚመለከታቸው የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች (እንደ የትምህርት ቤት አማካሪዎች ወይም ነርሶች) እንደአስፈላጊነቱ ሊካፈሉ እንደሚችሉ ተማሪዎች እንዲያውቁ ይደረጋል።ተማሪው በራሱ ወይም በሌሎች ላይ አደጋ እንዳለው ከገለጸ ወላጆች/አሳዳጊዎች ሁል ጊዜ ይነገራቸዋል።ተማሪዎች መጠይቁን ሲወስዱ መለያ ቁጥር(proxy ID) ይሰጣቸዋል፤በመጠይቁ ሂደት የተማሪ ስም ወይም የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪ መለያ ቁጥሮች ጥቅም ላይ አይውሉም።ከመጠይቁ የተገኘውን ስም አልባ  መረጃ የሚፈለጉትን ግብዓቶች ለመወሰን፣ አዝማሚያዎችን ለመለየት እና በ SBIRT ምላሽ ላይ አድልዎ ወይም ልዩነትን ለመመርመር ዓላማ  ከዲስትሪክት እና ከካውንቲ የ SBIRT ሰራተኞች ጋር ይጋራሉ።

**ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ውጤት እና የ SBIRT መረጃ እንዴት ይጠብቃል?**
የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የ SBIRT ሠራተኞች የተማሪን ግላዊነት በተለያዩ መንገዶች ይጠብቃሉ:

- ተማሪዎች የእራስህን  ፈትሽ መጠይቅ ሲወስዱ የተማሪው ትምህርት ቤት የ SBIRT ሰራተኞች ብቻ የሚያውቁት መለያ ቁጥር (proxy ID number) ይሰጣቸዋል።
- ተማሪዎቹ መጠይቁን በሚወስዱበት ጊዜ ግላዊነትን ለመጠበቅ በክፍል ውስጥ ተራርቀው እንዲቀመጡ ሆኖው በክፍል አስተማሪ እና በ SBIRT ሰራተኞች ክትትል ይደረግባቸዋል።
- አንድ ተማሪ መጠይቁን በሚወስድበት ጊዜ ስሙን ወይም ሌላ መለያ መረጃ ካስገባ፣የ SBIRT ሰራተኞች መለያውን ከስርዓቱ ለማስወጣ ይሰራሉ።
- የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የ SBIRT ሠራተኞች የተማሪዎችን ሚስጥር እና ልዩነት ይጠብቃሉ።አፋጣኝ የደህንነት ስጋት ከሌለ በስተቀር ተማሪዎች መጠይቁን ከወሰዱበት በተለየ ጊዜ ከ SBIRT ሰራተኞች ጋር እንዲገናኙ ይጠራሉ።
- ደህንነቱ የተጠበቀ፣በይለፍ ቃል የተጠበቀ፣ የዳታ ዳሽቦርድ (Tickit Health) የማን መሆኑን የማይታወቅ የ SBIRT መረጃ ይይዛል።

**ስለ የራስህን ፈትሽ ፈተና እና የ SBIRT ፕሮግራም ቤተሰቦች እንዴት ይነገራቸዋል?**
እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ከሚመለከታቸው ህጎች እና የሲያትል ትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲዎች* ጋር በሚጣጣም መልኩ የራሳቸውን የቤተሰብ ተሳትፎ እቅድ ያዘጋጃሉ እንዲሁም ይተገብራሉ*። የSBIRT ተሳትፎ ተግባራት በስርአተ ትምህርት ምሽቶች፣በቤተሰብ ትምህርት ዝግጅቶች፣እና በት/ቤቶች እና በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ድረ-ገጾች ላይ ይለጠፋሉ። ቤተሰቦች በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ በሚላከው የት/ቤት መጀመርያ ፓኬት እና የተማሪው የፍተና ቀን ከመድረሱ ከአንድ እስከ ሁለት ሳምንታት ቀደም ብሎ ፕሮግራሙን በሚመለከት በቀጥታ የጽሁፍ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል።በተጨማሪም፣የልጃቸው ውጤት ከፍተኛ የደህንነት ስጋትን የሚያመለክት ቤተሰቦች ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል።

* እዚህ የሚካተቱ:የተማሪ መብት ጥበቃ ማሻሻያ (PPRA)፤የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ (FERPA)፤ቦርድ ፖሊሲ 3232 የወላጅ/አሳዳጊ እና የተማሪ የዳሰሳ ጥናቶች፣ትንተናዎች ወይም ግምገማዎች አስተዳደር መብቶች፤ ቦርድ ፖሊሲ 2145  የራስን ማጥፋት መከላከል። ለበለጠ መረጃ የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች መከላከል እና ጣልቃገብነት ፕሮግራምን ያነጋግሩ።